በደ/ም/ኢ/ሕ/ክ/መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ
የሥነ-ህዝብ ልማት ትምህርት
ቅስቀሳ ዳይሬክቶሬት



Have the NUMBER of CHILDREN you can FEED , CLOTHE and EDUCATION

ቡክሌት. ቁ.01

ነሐሴ 2018 ዓ/ም
ሚዛን አማን


World Population
Projected world population until 2100
1990
5.3 billion
2015
7.3 billion
2030
8.5 billion
2050
9.7 billion
2100
11.2 billion
Source: United Nations Department of Economic and Social Affairs, Population Division, World Population Prospects: The 2015 Revision
Produced by: United Nations Department of Public Information
2015
TIME FOR GLOBAL ACTION

መግቢያ

የአንድን ሀገር ጤናማና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ ምቹና ከልማት ጋር የተመጣጠነ የህዝብ ቁጥር እድገት መኖር ወሳኝ ነው።

ስለሆነም የህዝብ ቁጥር እድገትን ከልማት እድገት ጋር ለማስተሳሰር በስነ-ህዝብና ልማት ችግሮች ዙሪያ የማህበረሰቡን አስተሳሰብና አመለካከት መቀየር ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው።

በመሆኑም የህዝብ ቁጥርን ከልማት ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ ለዜጎች (በተለይም ለተማሪዎች) ስለቤተሰብ ዕቀድ፤ስለ-ህገ ወጥ ስደት አስከፊነት፤ጥንቃቄ የጎደለው ወሲብ አስከፊነት፤ስለ አካባቢ ጥበቃ እና ስለሌሎችም የስነ-ህዝብ ችግሮች የማስገንዘብ ስራ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል።

ይህንን ስራ ለመስራት የስነ-ህዝብ ክበባት በትምህርት ቤቶችና በማህበረሰብ ውስጥ የስነ-ህዝብ ጉዳዮችን ለማስተዋወቅና ግንዛቤ ለማሳደግ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑ ይህ የግንዛቤ ማስጨበጫ ቡክሌት ተዘጋጅቷል።

የማስተማሪያ ሰነዱ አላማ

- ተማሪዎች ስለ ስነ-ህዝብና ልማት በቂ ግንዛቤ ይይዛሉ
- በህዝብ እድገትና በልማት መካከል ያለውን ትስስር ያብራራሉ
- ዋናዋና የስነ-ህዝብና ልማት ችግሮችን ይለያሉ
- ለችግሮቹ ተግባራዊ መፍትሄዎችን ይጠቁማሉ

1. ስነ- ህዝብና ልማት

- **ህዝብ** ማለት በአንድ ተከልሎ በታወቀ አካባቢ ወይም ድንበር ተለይቶ በተወሰነ ጊዜ የሚገኙ ነዋሪ ሰዎችን የሚወክል ነዉ።
- **ሥነ-ህዝብ** ማለት የአንድ ሀገር ህዝብ የተለያዩ ገጽታዎች ውልደት፣ሞትና ፍልሰት በመተንተን ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት በተለይም ለሰው ልጅ ኑሮ ከሚያስፈልጉ ሀብቶች ጋር በማገናዘብ የሚተነትን የዕውቀት ዘርፍ ነው።
- ልማት: ማለት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በቴክኖሎጂ እና በአካባቢ ጥበቃ ዘርፎች የሚታይ አጠቃላይ ዕድገት ሲሆን ሕዝብ ከልማት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላለው፣ ዘላቂነት ያለው ልማት ለማምጣት በሚደረገው ሂደት የህዝብ ጉዳይ ከጥራትና አቅርቦት ጋር በቅርበት የሚታይ ነው።

በመሆኑም የህዝብና ልማት ትስስርን ለማጠናከር መዋቅራዊ ሰነዶችና ጥናቶች ወሳኝ ናቸው። ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር የማይመጣጠን የህዝብ ቁጥር እድገት የምግብ፣ የመኖሪያ፣ የጤና እና የትምህርት አገልግሎቶች አቅርቦት እጥረት እንዲፈጠር ከማድረጉም በላይ፣ የተፈጥሮ ሀብት በፍጥነት እንዲመናመን ያደርጋል።

2. የክልሉ ሕዝብ ቁጥር ዕድገት አጠቃላይ ሁኔታ

የ1999 ዓ.ም የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤትን መሰረት በማድረግ በተደረገው ትንበያ፡

⇒ በ2018 ዓ.ም የክልሉ ህዝብ ብዛት 4,079,414 እንደሚሆን ይገመታል።ከዚህም

- ወንድ: 2,035,996 (49.9%)
- ሴት: 2,043,418 (50.1%)
- የመኖሪያ አካባቢ: በገጠር 83.8% እና በከተማ 16.2%
- የህዝብ ጥግግት: በአማካይ በ1 ካሬ ኪሎ ሜትር መሬት 104 ሰዎች ይኖራሉ።

⇒ **የዕድሜ ስብጥር ስንመለከት**

- ከ0-14 ዓመት: 1,998,353 (49%)
- ከ15-29 ዓመት: 1,115,911 (27.4%)
- ከ30-64 ዓመት: 879,042 (21.5%)
- ከ65 ዓመት በላይ: 86,108 (2.1%)

በአጠቃላይ ከክልሉ አጠቃላይ ህዝብ ከ0-29 ዓመት ያሉ ህጻናት እና ወጣቶች ድርሻ 3,114,264 (76.34%) መሆኑ ለወደፊት የመዋለድ አቅሙ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል።ይህንን ወጣት ኃይል በትምህርትና ስልጠና በማብቃት በሁሉም ዘርፍ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ ማድረግ ከተቻለ በክልሉ በሁሉም ዘርፍ በሚደረገዉ የልማት እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት ይቻላል።

ነገር ግን ይህን ወጣት ኃይል በተገቢዉ ማብቃት ካልተቻለ ለሀገርም ሆነ ለክልሉ ትልቅ ስጋት ሊሆን ይችላል።

3. ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ያልተመጣጠነ የህዝብ ቁጥር ዕድገት የሚያስከትለዉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች

የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ተፈጥሮ ሀብት አቅም ጋር ተመጣጥኖ ሲሄድ ለልማት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል። ብዙ ሕዝብ ማለት ብዙ የሰው ኃይል፣ ትልቅ የሸማቾች ገበያ እና በምርት ላይ የሚሳተፍ የሰው ኃይል ማለት ነው። ነገር

ግን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከምግብ ምርት፣ ከሥራ ዕድል፣ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከመኖሪያ ቤት፣ ከመሠረተ ልማትና ከአጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገት በላይ በፍጥነት ከጨመረ፣ በሀገርና በማህበረሰብ ላይ ተደራራቢ ችግሮችን ሊፈጥር ይችላል። ከእነዚህም ዋናዎቹ የምግብ እጥረትና የአቅርቦት ማነስ፣ የኑሮ ውድነት፣ የእርሻ መሬት ጥበት፣ የአካባቢ መራቆት፣ የትምህርትና ጤና አገልግሎት ጥራት መቀነስና ሌሎችንም ችግሮች ያስከትላል።

3.1. ማህበራዊ ችግሮች፤-

⇒ **የመኖሪያ ቤት እጥረት**፡- የህዝብ ቁጥር ሲጨምር ለዜጎች በቂ የመኖሪያ ቤት ለማግኘት ያስቸግራል።

⇒ በትምህርት ዘርፍ፡- በቂ ትምህርት ቤቶች፣ መምህራንና የመማሪያ ቁሳቁሶች እጥረት ይፈጠራል።

⇒ **የጤና አገልግሎት ላይ ጫና ያሳድራል**፡- ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ከአቅማቸው በላይ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ማህበረሰቡ ተገቢውን የህክምና አገልግሎት እንዳያገኝ ጫና ያሳድራል

⇒ **የውሃና የንፅህና ችግር**፡- ንጹህ ውሀና የፍሳሽ ማስወገጃ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ማዳረስ ላይ ጫና ሊፈጥር ይችላል

⇒ **የወንጀልና የማህበራዊ ግጭት**፡- **የስራ አጥነትና** የአገልግሎት እጥረት ማህበራዊ ችግሮችን ሊያባብስ ይችላል

3.2 ኢኮኖሚያዊ ችግሮች

⇒ **የምግብ እጥረትና አቅርቦት ማነስ;-** የሕዝብ ቁጥር ከኢኮኖሚ ዕድገት፣ ከግብርና ምርታማነትና ከምግብ አቅርቦት በበለጠ ፍጥነት ሲያድግ የምግብ ፍላጎትና የምግብ አቅርቦት መካከል ልዩነት ሊፈጠር ይችላል።

ይህም የምግብ እጥረትን፣ የዋጋ መጨመርንና የምግብ ዋስትና ችግርን ያባብሳል።የሕዝብ ቁጥር በጨመረ ቁጥር ለምግብ የሚኖረው ፍላጎት ይጨምራል። ብዙ ሰዎችን ለመመገብ ብዙ እህል፣ ጥራጥሬ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ሌሎች ምርቶች ያስፈልጋሉ። የምግብ ምርት ከሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ተመጣጣኝ ካልሆነ የፍላጎትና የአቅርቦት ክፍተት ይፈጠራል። ይህም የምግብ ፍላጎት ከአቅርቦት ሲበልጥ የምግብ ዋጋ የመጨመር ዕድል ይኖራል። ስለሆነም በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ቤተሰቦች ላይ ከፍተኛ ጫና በመፍጠር ቤተሰቦች በገቢያቸው መጠን የሚችሉትን ምግብ ብቻ ለመግዛት ስለሚገደዱ ለተመጣጠነ ምግብ

እጥረት ይጋለጣሉ፡፡ይህም በተለይ በሕፃናትና እናቶች ላይ የጤናና የአካላዊ እድገት ችግር ሊያመጣ ይችላል፡፡

⇒ **የኑሮ ውድነት;-** የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ሲጨምር ለሸቀጦችና ለአገልግሎቶች የሚኖረው ፍላጎት ይጨምራል፡፡ አቅርቦቱ በህዝቡ ፍላጎት ልክ በተመጣጣኝ ፍጥነት ካልጨመረ የዋጋ ጭማሪን ሊያስከትል ይችላል፡፡ይህም የምግብ፣ የልብስ፣ የቤት ኪራይና የመኖሪያ ቤት፣ የነዳጅ፣ የመጓጓዣና የሌሎች የዕለት ተዕለት ፍጆታዎች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምርና የኑሮ ውድነት እንዲፈጠር በማድረግ ቁጠባና እንቨስትመንት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

⇒ **የእርሻ መሬት ጥበትና የአካባቢ መራቆት፡-** የሕዝብ ቁጥርና የቤተሰብ ብዛት ሲጨምር የእርሻ መሬት በቤተሰብ ቁጥር ሊከፋፈል ይችላል፡፡ በዚህም አንድ ቤተሰብ የሚጠቀምበት የእርሻ መሬት መጠን እየቀነሰ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ ይህም የእርሻ መሬት ጥበትንና፣ መሬትን ከመጠን በላይ መጠቀምን(መሬቱ በቂ ጊዜ ሳያገኝ በተደጋጋሚ መታረስን) በመጨረሻም የመሬት ምርታማነት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡
ከዚህ በተጨማሪም የሕዝብ ቁጥር መጨመር የእርሻ መሬት ፍላጎትን ያሳድጋል፡፡ በዚህም ደኖች ወደ እርሻ መሬትነት ሊቀየሩ ይችላሉ ይህም የላይኛው የአፈር ክፍል በውሃና በነፋስ እንዲወሰድ በማድረግ የአፈር ለምነት እንዲቀንስና የመሬት መሸርሸር እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

⇒ **የመንግሥት ወጪ ከፍተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡-** መንግስት ለትምህርት፣ ጤና፣ መንገድ፣ ውሃና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን ለህዝቡ ለማቅረብ ከፍተኛ ወጪ ያስፈልጋል፡፡

⇒ **ስራ አጥነት፡-** በከፍተኛ ፍጥነት የሚያድግ የህዝብ ቁጥር ከሚፈጠሩ የሥራ እድሎች በላይ የሥራ ፈላጊዎች ቁጥር ከፍተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ይህም አዳዲስ የስራ ፈላጊዎችን ወደ ገበያዉ በማስገባት የስራ ስራ አጥነትን በከፍተኛ ሁኔታ ልያባብስ ይችላል፡፡

በአጠቃላይ፣ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እድገት ከተገቢዉ የኢኮኖሚ ዕድገትና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ጋር ካልተመጣጠነ፣ ድህነትን፣ ሥራ አጥነትን፣ የአገልግሎት እጥረትንና ሌሎችንም ችግሮች ያስከትላል

<u>የመወያያ ሀሳቦች፤</u>

- በቀበሌአችሁ የህዝብ ቁጥር ዕድገት ያስከተለዉ ምን አሳሳቢ ችግር አለ? ችግሩን አንድ በአንድ በማንሳት ተወያዩበት
- በቀበሌአችሁ ከአሁን በፊት የነበረዉን የህዝብ አሰፋፈርና የተፈጥሮ ሀብት (የአፈር ለምነት፣ ደን፣ የዱር እንስሳት፣ የእህል ምርት) አሁን ካለዉ ጋር አወዳድራችሁ በልዩነቱ ላይ ተወያዩ)

4. ስነ-ህዝብና አካባቢ ጥበቃ

- **አካባቢ ማለት፡-** በምድር ላይ የሚገኙ ህይወት ያለውንና ህይወት የሌለውን ነገር ሁሉን የሚያካትት ሲሆን ይሄውም በአየር፣ በውሀ አካለት፣በመሬት....ወዘተ ላይ የሚኖሩ ናቸው፡፡
- **የአካባቢ ጥበቃ፡-** ከላይ ለተዘረዘሩት የሚደረግ ጥበቃና እንክብካቤ ሲሆን በአካባቢ ውስጥ የሚገኙና የሚኖሩ የተለያዩ ፍጥረታትን ማለትም ሰዎችን፣ እንስሳትን፣ እጽዋትን፣ ደኖችን እናየውሀ አካላትን (ውቅያኖስ፣ ባህር፣ ሀይቅ፣ ምንጭ፣ ኩሬ ወዘተ...) እና የአየር ንብረትን ከተለያዩ ብክለቶችና የብክለት መንስኤዎች በመለየትና መፍትሄዎችን በማዘጋጀት በተገቢው ሁኔታ የመጠበቅ ሂደት ነው፡፡
- **የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች፡-** ዛፎችን መትከልና ደንን መጠበቅ፣ ቆሻሻን በአግባቡ መሰብሰብና መልሶ መጠቀም፣ ዉሀን ከብክለት መጠበቅና በቁጠባ መጠቀም፣የዱር እንስሳትንና እጽዋትን መጠበቅ፣ አየርን ከጭስና ጎጂ ጋሶች መጠበቅ፣ ማህበረሰቡን ስለአካባቢ ጥበቃ ማስተማርና የመሳሰሉት ዋና ዋና የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ናቸዉ፡፡
- **የአካባቢ ብክለት፡-** የአካባቢ ብክለት ማለት የአየር፣ዉሀ ወይም አፈር በጎጂ ነገሮች ሲበከልና በሰዉ በእንስሳትና እጽዋት ላይ ጉዳት ሲደርስ ማለት ነዉ፡፡
  - **የአካባቢ ብክለት አይነቶች፡-**
- **የአየር ብክለት፡-**ከተሽከርካሪዎች፣ ከፋብሪካዎችና ከተቃጠለ ቆሻሻ በሚወጣ ጭስ የከባቢ አየር ሲበከል፣
- **የዉሀ ብክለት፡-** ቆሻሻና የፋብሪካ ፍሳሽ ወደ ተለያዩ የዉሀ አካላት ሲገቡ የዉሀ ብክለት ይከሰታል፣
- **የአፈር ብክለት፡-** ፕላስቲክ፣ኬሚካሎች የመሳሰለ ቆሻሻ አፈር ላይ ሲጣል የአፈር ብክለትን ያስከትላል
- **የድምጽ ብክለት፡-**ከፍተኛ ድምጽ በሰዎችና እንስሳት ላይ ጉዳት ሲያደርስ ሲሆን በአጠቃላይ አካባቢ ብክለትን ለመቀነስ ቆሻሻን በአግባቡ መጣል እና የተለያዩ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡

- **የአፈር ብክለት፡-** ፕላስቲክ፣ ኬሚካሎች የመሳሰለ ቆሻሻ አፈር ላይ ሲጣል የአፈር ብክለትን ያስከትላል፣

- **የድምጽ ብክለት**፡-ከፍተኛ ድምጽ በሰዎችና እንስሳት ላይ ጉዳት ሲያደርስ ሲሆን በአጠቃላይ አካባቢ ብክለትን ለመቀነስ ቆሻሻን በአግባቡ መጣል እና የተለያዩ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡
- **የአየር ንብረት ለውጥ**፡- ማለት አንድ አካባቢ ከዚህ በፊት ከሚያገኘው የአማካይ ሙቀት፣ ዝናብ፣ የንፋስ መጠንና የመሣሰሉት በላይ ወይም በታች ሲያገኝ ማለት ነው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ በየአካባቢያችን እየተከሰተ ለመሆኑ በተለያዩ ቦታዎች ከፍተኛ ማሳያ ቀድሞ ደጋማ አካባቢዎች የነበራቸው ሙቀት በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ፤ከፍተኛ የሆነ ሙቀትና ጎርፍ እያስከተለ መታየቱ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተፈጥሮ አደጋዎችን ማለትም የድርቅ፣የወበቅ ክስተትን የበረሃማነት መስፋፋት እንዲሁም የተለያዩ የጤና ችግሮችን እያስከተለ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ እየሆነ የመጣ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ችግር የሚከሰተዉ በዋናነት በከፍተኛ ሁኔታ የህዝብ ቁጥር መጨመሩን ተከትሎ የመሬት መራቆት ጉዳይ ነው፡፡

ይህ ማለት የህዝብ ቁጥር መጨመርን ተከትሎ ለእርሻ መሬቶችና ለመጠለያ ፣ለኃይል ፍጆታ(ከሰልና ማገዶ እንጨት)፣ ለገቢ ማስገኛ እና ለእንስሳት የግጦሽ መሬት የመሳሰሉት ደንን እና የደን ዉጤቶችን የመጠቀም ፍላጎት ከፍተኛ መሆን በደን የተሸፈነ አካባቢ እንዲራቆትና የደን ሀብቱ እንዲመናመን ስለሚያደርግ የአየር ንብረት ለውጥ ይከሰታል፡፡

♦ ይህን ችግር ለመፍታት፣-

- በተፋሰስ ሥራዎች የተራቆቱ አካባቢዎችን ማልማት
- የህብረተሰቡን የአማራጭ ኢነርጂ ተጠቃሚነት ማሳግ
- የኑሮ መሰረታቸዉ ከደን ዉጤት ጋር ለተቆራኘ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ዘርፎች እንዲሳተፉና እንዲጠቀሙ ማድረግ
- ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም

- ማህበረሰቡ ገቢዉን ያገናዘበ የቤተሰብ ቁጥር እንዲኖረዉ በቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ላይ ግንዛቤ መፍጠር እና ተጠቃሚ ማድረግ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች የመፍትሄ አማራጮችን መጠቀም ካልተቻለ አሁን ካለዉ የህዝብ ቁጥር እድገት አንጻር በአካባቢ ጥበቃ ላይ እየተሰሩ ያሉ ተግባራት ዉጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች የነገ የሀገር ተረካቢ ዜጎች እንደመሆናችው ጤናማ ትውልድ እንዲኖረን ጤናማ አካባቢን ፈጥረን ማስረከብ ይኖርብናል ለዚህም የችግሩ ተጠቂ እንዳንሆን የመፍትሄዉም ባለቤት በመሆን ተማሪዎች በየአደረጃጀቱ በጋራ በመመካከር የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ በሚያስችል መልኩ ሊወያዩ ይገባል፡፡



ስዕል 1 ዛፎችን ያለአግባብ መቁረጥ የደን መመናመንን ያስከትላል

➢ የመወያያ ነጥቦች

- ከህዝብ ቁጥር እድገት ጋር ተያይዞ በአካባቢያችሁ ያለዉ የደን ውድመት ያስከተለዉ ችግር ምንድነዉ? ችግሩን ለመቅረፍ ከህብረተሰቡ ምን ይጠበቃል?
- በአካባቢያቸው የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተላቸዉ ችግሮችስ ምን ምን ናቸው? ለነዚህ ችገሮች የተማሪዎች ድርሻ ምንድን ነው? በቀጣይስ ይህንን ችግር ለመፍታት ከተማሪዎች ምን ይጠበቃል?
- በት/ቤታችሁ ስለ አየር ብክለት መንስኤ ግንዛቤው አላችሁ? ተወያዩበት
- ለአካባቢያችን የተፈጥሮ ሀብት መመናመንና መራቆት መፍትሄው ምንድነው ትላላችሁ?ተወያዩበት

5. ወጣቶችና ተዋልዶ ጤና

ተዋልዶ ጤና ሁሉንም ተዋልዷዊ ጤንነትን የመንከባከብ፣ በዚህም ዘርፍ ተገቢውን መረጃና አገልግሎት የማግኘትና ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የማስወገድ ጽንሰ-ሀሳብ የሚይዝ ነው፡፡ የወጣትነት ዕድሜ ክልል ፈጣን አካላዊና አዕምሮአዊ ለውጥ የሚከሰትበት፣

የወጣትነት አዕምሮ የሚበስልበት፣ አካላዊ ዕድገት የሚዳብርበት፣ ለማህበራዊ ኑሮ የሚያበቃ መሠረት የሚጣልበት፣ ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት መሸጋገሪያ የቤተሰብና የማህበረሰብ ኃላፊነቶችን ለመቀበል ዝግጅት የሚጀመርበት ወቅት ነው፡፡ ይህ ዕድሜ ፈጣን አካላዊና አዕምሮአዊ ለውጥ የሚከሰትበት እንደመሆኑ ወጣቶች የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎትና መረጃ መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ መገናኛ ዘዴዎች ሊሰራጭላቸውና ራሳቸውን ከማንኛውም የተዋልዶ ጤና ችግሮች የሚከላከሉበት ሁኔታ ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡

5.1 በወጣቶች ላይ የሚከሰቱ የተዋልዶ ጤና ችግሮች

ወጣቶች በጉርምስናና በኮረዳነት ወቅት በአካላቸው ላይ የተከሰቱትን ለውጦችና በየታቸው መካከል ያለውን ልዩነት በመገንዘብ ጾታዊ ግንኙነት ለመፈፀም ፍላጎት ያድርባቸዋል፡፡ነገር ግን እነዚህ ወጣቶች ስለ ጾታዊ ግንኙነት ያላቸው ዕውቀት በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ግንኙነት የሚፈፅሙት ጥንቃቄና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ባለመሆኑ፡-

- ለአባለዘር በሽታዎችና ኤች አይ ቪ/ኤድስ
- ላልተፈለገ እርግዝናና ለውርጃ በቀላሉ ሊጋለጡ ይስተዋላል፡፡

በተሻሻለው የኢትየጵያ የቤተሰብ ህግ መሰረት የሴቶች የጋብቻ ዕድሜ 18 ዓመት ነዉ፡፡ በለጋ ዕድሜ የሚያገቡ ሴቶች ካረገዙ የእናቶችና የህፃናት ሞትን ጨምሮ ከወሊድ ጋር የተያያዙ ውስብስብ የጤና ችግሮች ለምሳሌ፤ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ምጥ፤ ፊስቱላና ብዙ የደም መፍሰስና ሞት የመሳሰሉት ችግሮች ያጋጥማቸዋል፡፡

በለጋ ዕድሜ ለሚከሰት ያልተፈለገ ዕርግዝና ምክንያቶቹ፡-

- ስለፅንስ መከላከያ ዘዴዎች ያለው ዕውቀት ማነስና አገልግሎቱንም ማግኘት ያለመቻል፤
- አደንዛዥ ዕፆችን መውሰድና አልኮል መጠጣት፤
- ልቅ የወሲብ ባህሪያት መስፋፋት፤
- የአቻ ጓደኛ ግፊት፤
- ያለእድሜ ጋብቻ፤

- ጠለፋና አስገድዶ መድፈር የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው፡፡

ከዚህ አኳያ ለወጣቱ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ዖታዊ ግንኙነትን የሚመለከቱ ትምህርቶችንና መረጃዎችን በቀላሉ በመስጠት በለጋ ዕድሜ የሚደርሰውን ያልተፈለገ ዕርግዝናና ውርጃን በአብዛኛው መከላከል ይቻላል፡፡

5.2 የተዋልዶ ጤና መብቶች

ተዋልዶ ጤና ማለት ከመራቢያ አካላት ሥርዓት፤ ተግባርና ሂደት ጋር በተያያዘ የተሟላ የአካል፣ የአእምሮና የማህበራዊ ህይወት ደህንነትን መጐናፀፍ እና ከተዋልዶ ሥርዓት ሂደት ጋር በተያያዘ ከሚከሰቱ ህመሞች ነፃ መሆን ነው፡፡ የተዋልዶ ጤና በአንድ በኩል ከተዋልዶ ጤና ጋር ተዛማጅ የሆኑ ህመሞችን ማለትም የአባላዘር በሽታዎችን፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስንና በመዋለጃ አካላት ላይ የሚከሰቱ የካንሰርና ሌሎች ህመሞችን ማከምና በሌላ በኩል ከወሊድ ጋር ተያያዥ የሆኑ ተፈጥሮአዊ ሂደቶችን ማለትም ጤናማ የግብረ ስጋ ግንኙነትንና፣ እርግዝናን፣ ወሊድን፣ ድህረ-ወሊድን፣ ውርጃንና መካንነትን የመሳሰሉት ሁኔታዎችን ያካተተ ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡

በአጠቃላይ በእርግዝናና ወሊድ ወቅት ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት የማግኘትና ጤናማ ልጅ የመውለድ፣ የልጆች መጠንና የሚወልዱበትን የጊዜ ርቀት የመወሰን፣ በግብረ-ስጋ - ግንኙነት አማካይነት የሚተላለፉ በሽታዎችን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ጨምሮ የመከላከልና የመታከም፣እንዲሁም የተሟላና ወቅታዊ የሆነ የቤተሰብ ዕቅድ መረጃና የምክር አገልግሎት የማግኘት መብትን ያጠቃልላል፡፡ የተዋልዶ ጤና መብቶች ተብለው ከሚጠቀሱት መካከል፡-

5.2.1. በህይወት የመኖር መብት፡-

በህይወት የመኖር መብት በግፍ ወይም በወንጀል መልክ ህይወትን ከማጣት ጋር ብቻ ተያይዞ መታየት የለበትም ከተዋልዶም አኳያ ይህ መብት ተገቢውን ግንዛቤ አግኝቶ አስፈላጊው ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡እናቶች አዲስ ህይወትን ወደዚህች ዓለም ለማምጣት ሲሉ የገዛ ህይወታቸውን አደጋ ላይ መጣል ወይም ማጣት የለባቸውም

5.2.2 የጤና ክብካቤ የማግኘት መብት፡-

ይህ መብት በህይወት የመኖር መብት ጋር በጥብቅ የተገናኘ ነው፡፡መንግስት የዜጎችን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ የበሽታ መከላከል ተግባራትን ከማከናወን በተጨማሪ

የህክምና አገልግሎቶችን ማዳረስ እንደሚገባ የሚያመላክት ነው። በእነዚህ የህክምና ተቋማት ባለትዳሮችና ግለሰቦች የተዋልዶ ጤና አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ የማግኘት መብት አላቸው።

5.2.3. የግል ሚስጥር የተጠበቀ የመሆን መብት፡-

ከህክምና ወይም ከተዋልዶ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ተገልጋዮች የግል ሚስጥራቸውን ለባለሙያዎች የሚያካፍሉበት ሁኔታ መኖሩ ይታወቃል። ባለሙያዎች የምክር ወይም የህክምና አገልግሎት ሲሰጡ በስራ ባህሪያቸው ምክንያት ያወቁትን የግል ሚስጥር በምንም አይነት ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን አሳልፈው መስጠት አይኖርባቸውም።

5.2.4 የወጣቶች ተዋልዶ ጤና አገልግሎት የማግኘት መብት፡-

የቤተሰብ እቅድን ጨምሮ የተዋልዶ ጤና መረጃዎችን ትምህርቶችንና አገልግሎቶችን ለአዋቂዎች ብቻ ሳይሆን ለወጣቶችም ማዳረስ አስፈላጊ ነው ለወጣቶች ተለይተው አገልግሎት እንዲሰጡ ታስበው የተቋቋሙ የተዋልዶ ጤና መስጫ ተቋማት ከቁጥር የሚገቡ አይደሉም። በዚህም የተነሳ በወጣቶች ዘንድ ያልተፈለገ እርግዝና ይከሰታል እንደዚህ አይነት ሁኔታ መከሰት ደግሞ ህገ-ወጥና ንፅህናው ያልተጠበቀ እንዲሁም ህይወትን ለአደጋ የሚያጋልጥ የፅንስ ማቋረጥ ተግባር ውስጥ ወጣቶች እንዲገቡ ያደርጋል።

እነዚህን ሁኔታዎች ለመቅረፍና ህብረተሰቡ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ አሁንም ጥረት ማድረግ ይጠበቃል።

5.2.5 የግልነፃነትና የደህንነት መብት፡-

ይህ መብት ከተዋልዶ ጤና አኳያ ሲታይ ሰዎች ወሊድንና የመዋለጃ አካለቸውን በሚመለከት ወሳኞቹ ራሳቸው እንጂ ሌላ ሶስተኛ ወገን አለመሆኑን አፅንኦት የሚሰጥ ጉዳይ ነው።ሰዎች የትዳር ጓደኞቻቸውን የመምረጥ ጋብቻ የመፈፀም ወይም ያለመፈፀም ልጅ የመውለድ ወይም ያለመውለድ የልጆቻቸውን ብዛት የመወሰን አቅዶ የመውለድና የመሳሰሉ ግላዊ ነፃነቶችና መብት አላቸው።እነዚህ መብቶች በጎጂ ልማዳዊ

አስተሳሰቦችና ድርጊቶች እንዲሁም በሌሎች መሰል ምክንያቶች የተነሳ ሲጣሱ ይስተዋላል፡፡በአንዳንድ አካባቢዎች ያለተጋቢዎቹ ፈቃድ እና ዕውቅና በቤተሰብ ስምምነት ብቻ ጋብቻ ሲፈጸም ይታያል፡፡የሴት ልጆች ግርዛት ልጆች ባላወቁበትና ባልፈቀዱበት ሁኔታ የሚፈፀም የመብት ጥሰት ድርጊት ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ የተዋልዶ ጤና መብቶች ስምምነት ተቀብላ አፅድቃለች በተጨማሪም በአገራቱ የጤና ተቋማትን በማስፋፋት የሰለጠነ የሰው ሀይል በማሟላት የተዋልዶ ጤና መብቶች እንዲጠበቁ አገልግሎቶችም በተጠናከረ መልኩ እንዲሰጡ ጥረቶች በማድረግ ላይ ነው የመብት ጥሰቶችም ሲኖሩ ህጋዊ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል፡፡

የመወያያ ርዕሰ-ጉዳዮች

1. በአካባቢያችሁ በወጣቶች ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ምንድናቸው?
2. በአካባቢያችሁ የወጣቶች ማዕከላት አሉን?
3. የአካባቢው ወጣቶች በማዕከላቱ የመጠቀም ልምድ አላቸው?
4. በአካባቢያችሁ ያለዕድሜ በማርገዝ የተከሰቱ ችግሮች አሉን? ካሉስ እንዴት ተቃለለ?
5. በአካባቢያችሁ ባልተፈለገ ዕርግዝናም ሆነ ያለዕድሜ በማርገዝና በመውለድ ከቤተሰቦቻቸው የጠፉ ሴት ልጆች ይኖራሉ?
6. በአካባቢያችሁ በወጣቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ በተለይም ጥንቃቄ ስለተሞላበት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከልጆች ጋር ግልፅ ውይይት ይደረጋል?

ግልፅ ውይይት የማይደረግ ከሆነ ከአሁን ጀምሮ ውይይት ማድረጉ ቢለመድ ይጠቅማል ወይስ ይጎዳል?

በአካባቢያቹ ከተዋልዶ ጤና ምንነት ጋር ተያይዞ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የሚሰጡ ተቋማት አሉ? የሚሰጡትን ትምህርቶች ህብረተሰቡ በተገቢው ተረድቶ እየተገበረው ነው?

በአካባቢያችሁ ከተዋልዶ ጤና ጋር የተያያዘ የመብት ጥሰቶች አሉ? ህብረተሰቡ እነዚህን የመብት ጥሰቶች ለማስቀረት ምን ይጠበቅበታል?

6. ቤተሰብን ማቀድ

- **ቤተሰብ ማለት፡-** በጋብቻ፣በደም ዝምድና ወይም በጉዲፈቻ ግንኙነት የሚጣመሩ እና በአንድ ላይ የሚኖሩ የህብረተሰብ መሰረታዊ ክፍል ነዉ፡፡
- **የቤተሰብ እቅድ(Family planning) ማለት፡-**_ ጥንዶች(ባለትዳሮች) አቅምን ገቢን ባገናዘበ ሁኔታ መቼ ልጅ መውለድ፤ ስንት ልጆች መውለድ፤በስንት ዓመት የዕድሜ ልዩነት መውለድ እንደሚፈልጉ የሚወስኑበትና እንዲሁም የቤተሰብም ሆነ የልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ሲሆን ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ በልዩ ልዩ የጽንስ መከላከያ ዘዴዎች በመጠቀም የተሻለ ኑሮ ለመምራት ያስችላል፡፡
- **የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ዘዴዎች የት ይገኛሉ?፡-** ያልተፈለገ ጽንስ እንዳይፈጠር ለመከላከል የምንጠቀማቸው ልዩ ልዩ ሳይንሳዊ ዘዴዎች በተለያየ መንገድ የተዘጋጁ ሲሆን አገልግሎታቸውና ዉጤታማነታቸውም አንዱ ከሌላው የተለያዩ ሆነው ለተጠቃሚዎች የተለያየ ምርጫ እንዲኖራቸው በማድረግ ተዘጋጅተው በአቅራቢያዎ በሚገኘው በጤና ተቋማት፣በተለያዩ የመድሃኒት ቤቶችና ክሊኒኮች ይገኛሉ፡፡

6.1. ቤተሰብን ማቀድ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች

- የእናትና የልጅን ጤና ለመጠበቅ ይረዳል
- በወሊድ መካከል በቂ ጊዜ እንዲኖር ያግዛል
- የቤተሰብን የኢኮኖሚ ሁኔታ በተሻለ ለማቀድና ለመምራት ያስችላል
- ያልተፈለገ እርግዝናን ለመቀነስ ይረዳል
- ወላጆች ስለልጆች ቁጥርና የመዉለድ ጊዜ በጋራ እንዲወስኑ ያስችላል
- በእቅድ ከገቢ አቅም ጋር ተገናዝቦና ተፈልገው የተወለዱ ልጆች በቂ እንክብካቤ፤ ምግብ፤ ትምህርት፤ ልብስና፤ ፍቅር አግኝተው ስለሚያድጉ ጤነኛ ጠንካራና ደስተኛ ዜጋ ሆነው እንዲያድጉ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡
- ቤተሰብን ማቀድ ለሀገር የህዝብ ቁጥር እድገትን በአግባቡ ለመቆጣጠር ይረዳል
- የጤና የትምህርትና ሌሎች መሠረተ ልማቶችን በጥራት ተደራሽ እንዲሆኑ ያስችላል
- ድህነትን ለመቀነስ እና የኑሮ ደረጃን ለማሻሻል ያግዛል
- እንደ ሀገር ዘላቂ ልማትን ለማሳካት አስተዋጽ

በአጠቃላይ ቤተሰብን ማቀድ ጤናማ የተረጋጋና አቅምን ያገናዘበ ቤተሰብ ለመገንባት ከማስቻሉም በላይ የሀገርን ሀብት ፣ኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት በተሻለ ሁኔታ ለማስተዳደር ይረዳል፡፡

የመወያያ ርዕሰ-ጉዳዮች፤

1. **ቤተሰብ ማለት ምን ማለት ነዉ?**
2. **የቤተሰብ እቅድ ጠቀሜታዎች ላይ ተወያዩ?**
3. **የቤተሰብ እቅድ ዘዴዎችን ዘርዝሩ?**



ስዕል 2 (ገቢን ያገናዘበ ቤተሰብ መመስረት ብልህነት ነው)!!!

3. **ወጣት ጥፋተኝነት** (juvenile delinquency)

ወጣት ጥፋተኝነት በህግ የተከለከለውን ተላልፈው የሚገኙትን ወይም በህግ የተከለከለውን ጥፋት ለመፈፀም የተዘጋጁትን እና ከአዋቂ ወንጀለኞች በተለየ ሁኔታ መያዝ ያለባቸውን ታዳጊ ህፃናትንና ወጣቶችን ያመለክታል። ለወጣት ጥፋተኝነት መነሻ ሁኔታዎችን ስንመለከት፡

- **ወጣቶች በአፍላ የጉርምስና ጊዜያቸው አንዳች ነገር አከናውነው ለመታወቅ የሚመኙ በመሆኑ፤**
- **የወጣትነት ዕድሜ ወጣቶች በራሳቸው ውሳኔ መንቀሳቀስና ነጻ መሆን የሚፈልጉበት ጊዜ በመሆኑ።**
- **ወጣቶች በባህሪያቸው አዲስ ነገርን የመሞከርና የማየት ጉጉትና ፍላጎት ስላላቸዉ የሚሞክሩት አዲስ ነገር አንዳንድ ጊዜ በህይወታቸው ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በአግባቡ ባለመረዳት ከፍተኛ ችግር ሊያደርሱ የሚችሉ ድርጊቶችን ይፈጽማሉ።**

በአሁኑ ወቅት በተጨባጭ እየታየ እንዳለው ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ወጣቶች አላስፈላጊ በሆነ የስብዕናና የሞራል ችግር ስር እየወደቁ ይገኛሉ፡፡

ለዚህ ችግር እንደ **ዋና ማባባሻ የሚጠቀሱ ምክንያቶች፡-**

- የቤተሰብ ችግርና የወላጆች ክትትል እጥረት
- ድህነትና ስራ አጥነት፣
- በየከተሞች ያሉ የሺሻ፣ የጫት ቤት፣ የምሽት ዳንስ ቤቶች መበራከት
- የአቻ ግፊት እና የስነ-ምግባርና የህግ ግንዛቤ እጥረት፣ የወጣቱ የስራ ባህል አናሳ መሆንና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ለወጣት ጥፋተኝነት መስፋፋት ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች የቤተሰብ ክትትል መላላት፣ ስራአጥነት፣ የገቢ ማነስና በቂ የመዝናኛ ስፍራዎች አለመኖር፣ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ትምህርት ማቋረጥ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት፣ የመጠጥና የመቃሚያ/ሺሻ ቤቶች መስፋፋት የት/ቤቶች ቁጥጥር አነስተኛ መሆን በቅደም ተከተል ለወጣት ጥፋተኝነት መንስኤዎች ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ የወጣት ጥፋተኞች ቁጥር እየጨመረ ይገኛል፡፡

ስለዚህ የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ የሆኑትን ወጣቶች በስነ-ምግባር ታንፀው ብቁ ዜጋ የማድረግ ሀላፊነት የሁላችንም ድርሻ ስለሆነ ተማሪዎች ወጣቶችን ለጥፋት የሚዳርጉ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት በማድረግ የመፍትሄው አካል ሊሆኑ ይገባል፡፡

የመወያያ ርዕሰ-ጉዳዮች

- በአካባቢያችሁ ወጣቶችን ለጥፋት የሚያጋልጡ ሁኔታዎች አሉ? ህብረተሰቡ ይህንን በምን መልኩ መከላከል አለበት ?
- የወጣት ጥፋተኝነት ለመቀነስ በቤተሰብና በህብረተሰብ ደረጃ መወሰድ ያለባቸው ጥንቃቄዎች ምን መሆን አለባቸው?

- በአካባቢያችሁ የወጣት ጥፋተኝነት እያስከተለ ያለው ጉዳት ካለ በምን አግባብ መስተካከል አለበት ትላላችሁ?



ስዕል 3 ለወጣት ጥፋተኝነት አጋላጭ ሁኔታዎች

4. ህገ-ወጥ ፍልሰት

ፍልሰት ማለት፡- ሰው በግልም ሆነ በጋራ በመሆን ከሚኖርበት አካባቢ ለቆ የተሻለ ኑሮ በመፈለግ ወደ ሌላ አካባቢ በዘላቂነት ወይም በጊዜያዊነት ለመኖር የሚደረግ የሰዎች እንቅስቃሴ ሲሆን ህገ ወጥ ፍልሰት ሰዎች የሚሄዱበትን ሀገር የሕግ መስፈርት ሳያሟሉ ወይም ያለ ተገቢ ፈቃድ ከአገር ወደ ሀገር መሻገር ነው። ይህም በግለሰብ፣ በቤተሰብና በሀገር ላይ የተለያዩ ችግሮችን የሚያስከትል ሲሆን በህገ-ወጥ ፍልሰት ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች፡-

- **የሕይወት አደጋ፡-** አደገኛ የጉዞ መንገዶችና ተሽከርካሪዎች ምክንያት ሞት ወይም ከባድ ጉዳት ሊደርስ ይችላል።
- **የሰው ዝውውርና ጉልበት ብዝበዛ፡-** ህገ ወጥ ፍልሰተኞች ለህገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች እና ለጉልበት ብዝበዛ ሊጋለጡ ይችላሉ።
- **የሥራ ችግር፡-** በሚደርሱበት አገር ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ ስለሌላቸው ለብዝበዛና ለዝቅተኛ ደመወዝ ሊጋለጡ ይችላሉ።

- **የቤተሰብ መለያየት፡-** ከቤተሰብ መራቅ፣ ግንኙነት መዳከምና ልጆች ያለ ወላጆቻቸው መቅረት ሊከሰት ይችላል።
- **የአእምሮና የማህበራዊ ጫና፡-** ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ ብቸኝነትና የማህበራዊ መገለል ሊከሰት ይችላል። በአጠቃላይ ህገ ወጥ ፍልሰት የሰውን ሕይወትና ደህንነት አደጋ ከማስከተሉም በላይ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።

የፍልሰት ዋና ዋና ምክንያቶች፡-

- የእርሻ መሬት እጦት እና የመሬት ይዞታ እያነሰ መሄድ፣
- የተፈጥሮ አካባቢ መጎዳትና ወቅቱን እየጠበቀ የሚከሰት ድርቅና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚከሰት ረሃብ፣
- ድህነት፣
- ስራ አጥነት፣
- ግጭትና የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ ያለመኖር ዋና ዋና ምክንያቶች ሲሆኑ በተለይም ከገጠር ወደ ከተማ እንዲሁም ከከተማ ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው።

የመወያያ ሀሳቦች

- የህገ-ወጥ ፍልሰት ምክንያቶች ምን ምን ናቸዉ?
- በአካባቢያችሁ ትምህርት በማቋረጥ ወደ ሌላ አካባቢ የሚሄዱ ተማሪዎች አሉ?
- ተማሪዎች ትምህርታቸዉን አቋርጠዉ በለጋ እድሜያቸዉ ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች እንዳይጋለጡ ምን መደረግ አለበት?



ስዕል 4 ህገ-ወጥ ፍልሰትና መዘዙ

5. ስርዓተ-ፆታ ምንነት ትንተና

ጾታ፡- ማለት ሰዎች በስነ ህይወት አፈጣጠራቸው የተነሳ በአካላዊ ይዘታቸው ላይ የሚያሳዩትን ልዩነት የሚያመለክት ነው፡፡ ይህን የተፈጥሮ ጸጋ በመወለድ የሚገኝና ተለዋጭ ያልሆነ የስነ ህይወት ባህሪ ነው፡፡

ሥርዓተ ጾታ፡- ስንል ማህበረሰቡ ለወንዶችና ለሴቶች በጾታቸው ምክንያት በሚሰጣቸው ቦታ፤ የሚጠበቅባቸውን የሥራ ድርሻ፣ ሀላፊነት፣ አመለካከትና ባህሪይ የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ የሥርዓተ ጾታ አመለካከት ተለዋዋጭ የሆነና ከባህል ባህል የሚለያይ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብና ድርጊት ህብረተሰቡን በተለይም ጾታን መሠረት አድርጎ ልዩነት መፈጠሩና ሴቶችን በልማት አጀንዳ ውስጥ ከዝግጅት ምዕራፍ እስከ ተጠቃሚነት በሚፈለገው ልክ እንዳይሳተፉ መደረጉ በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊ (በትምህርት፣ በጤና...) እና በፖለቲካዊ ዘርፍ እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል፡፡

- **በትምህርት ዘርፍ፡-** በትምህርት ዘርፍ በተሰሩ ስራዎች የሴቶች ተሳትፎ የተሻለ ውጤት እየታየ ቢሆንም በአንዳንድ ገጠራማና አርብቶ አደር አካባቢዎች ድህነት፣ ያለእድሜ ጋብቻ፣

  የቤተሰብ ኃላፊነት፣ የትምህርት ተደራሽነት እጥረትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሴቶችን ትምህርት ሊያደናቅፉ ይችላሉ

- **በኢኮኖሚ ዘርፍም፡-** ሴቶች በግብርና፣ በንግድና በተለያዩ የሥራ መስኮች ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ነገር ግን የመሬት፣ የካፒታል፣ የብድርና የሥራ እድል ተደራሽነት ችግሮች አሁንም ይታያሉ፡፡
- **በፖለቲካና በውሳኔ ሰጪነት ዘርፍ፡-** የሴቶች ተሳትፎ በመጨመር ላይ ቢሆንም፣ በሁሉም የአመራር ደረጃዎች እኩል ውክልና ማረጋገጥ ላይ አሁንም ክፍተቶች አሉ፡፡
- **በጤና ዘርፍ፦** የእናቶችና የሕፃናት ጤና አገልግሎት እየተሻሻለ ቢሆንም በተዋልዶ ጤናና በቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚነት ላይ አሁንም ችግሮች ይስተዋላሉ ::
- **ጾታዊና ጾታ-ተኮር ጥቃት፦** የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የጾታ ጥቃት፣ ያለ እድሜ ጋብቻና ሴት ልጅ ግርዛት የመሳሰሉት አሁንም ያልተቀረፉ ችግሮች ናቸዉ፡፡

በአጠቃላይ የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ የሴቶችን ትምህርት ማስፋፋት፣ የሥራና የኢኮኖሚ እድሎችን ማሳደግ፣ ሴቶችን በውሳኔ ሰጪነት ማበረታታት፣ ጾታ-ተኮር ጥቃትን መከላከልና ማህበረሰቡን ስለ ጾታ እኩልነት ማስተማር ያስፈልጋል።በአጠቃላይ የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ በተሰሩ ስራዎች መሻሻል ቢኖርም በሚፈለገዉ ልክ ዉጤታማ ለመሆን መንግሥት፣ ማህበረሰብ፣ ትምህርት ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በጋራ በመሥራት ሴቶችና ወንዶች እኩል መብትና እድል የሚያገኙበትን ማህበረሰብ መገንባት ይገባል።

የመወያያ ርዕሶች

- በአካባቢያችሁ ለሴትና ለወንድ የሚሠጠው ግምት ምን ይመስላል ?
- በአካባቢያችሁ ተግባርን ከመፈፀም አንፃር ሴት ልጆች ከወንድ ልጆች የሚለዩት በምንድ ነው?
- ሴት ልጆችን በቀጣይ እንዴት ማበረታታት ይቻላል?
- በቤት ውስጥ ቤተሰቦቻችሁ ለወንድና ለሴት ልጅ የሚሰጡት አመለካከት ደረጃ ምን ይመስላል?
- በአካባቢያችሁ በሴቶች ላይ ምን ምን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ይፈጸማሉ ?
- በአካባቢያችሁ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጾታዊ ጥቃት ላይ በዝርዝር ተወያዩ?









ለበለጠ መረጃ፤- ስልክ ቁ. 0991738085

ኢሜል –Southwest plan & Development
2017@gmail.com

Website: http:www.SWEPRSBOPD.gov.et